## ኦሮሞ ፓለቲካና የደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እጣ ፋንታ

## በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ ልብ ወለድ

## ክፍል ፯. ፫ የትም ወድቆ መቅረት፣ ካለፈው የቀጠለ

አባባ መቸም የማረሳው ለአባባ አለሙ ማመልከቻ ፅፌላቸው እንደጨረስኩ አንተ ፈንጠር ብለህ ደጀሰላሙ ፊት ለፊት ትጠብቀን ስለነበርን ወደአንተ መጣን። እሳቸው መርቀውኝ እንደተለያየን ወደቤታችን ሳንሄድ ትንሽ አረፍ እንድል ጠየቅከኝ። እሳቸው ከተለዩን በኋላ አንተ አለሙ የፈለገው ወደእነሱ ቤት እንድንሄድ ነበር። እሱ ያሰበው ማመልከቻውን ፅፌሽ ስታበቂ የምትወጅው እሸትም ስለደረሰ ሊጋብዝሽ ነበር። እኔ ግን ራሴ ብቻየን የማማክርሽ ነገር ስላለኝ ፀጥ ባለው ቦታ በቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ሆነን የማስበውን ነግሬሽ በዚያ ላይ እንድንነጋገር ስለፈቀድኩ እዚህ ቀጠርኩት አልከኝ። የቤተክርስቲያኑን ድባብና ፀጥታ፣ የአንተን ጭንቀት፣ የተነጋገርነውን ሁሉ ቃል በቃል አስታውሰዋለሁ። ምክንያቱም እኔ ስለጋረደብኝ ነው እንጅ የነገርከኝ ሁሉ አጥጋቢና ምክንያታዊ ነበር።

አባባ አሁን የምፅፍልህ እምባየ እየወረደ ነው። አንተ በኦሮሚያ ክልል ከቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ 3000 የአማራ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የተመለሱትን ልጆች ታሪክ በቅርበት ታውቅ ነበር። እኔ ተመልሸ ወደ ደምቢ ዶሎ ዩኒቨርስቲ እስከምመለስ ድረስ ከቡሌ ሆራ የተባረሩት ተማሪዎች፣ እኛ በቅርበት የምናውቃቸው አገሬና ፋንታሁን የት እንዳሉ አይታወቅም ነበር። ሁለቱም ከትምህርት ቤቱ ሲፈናቀሉ ለመመረቅ የቀራቸው ጊዜ 4 ወር ብቻ እንደነበርም አውቃለሁ። አንድ ሰሞን ተማሪዎቹ ባህርዳር ድረስ ተንከራተው ሄደው ሰላማዊ ሰልፍ ቢያደርጉም አዴፓ ከፍተኛ ማንገላታትና ወከባ እንደደረሰባቸው ተሰምቶም ነበር። አባቶቻቸው ባህርዳር ያሉ መስሏቸው ተንከራተው ሄደው አጥተዋቸው ተመልሰዋል።

አንተ ሌላም ሌሎቻችን የማናውቀው አገዛዙ ችግር አዘል እንደሆነ የሚያመላክት ብዙ ማስረጃ ነበረህ ። እኔ አልሰማም አልኩ እንጅ አንተ ልጅህንም ለማዳን ጥረት አድርገህ ነበር። በቤተክህነት በኩልም እስከዚያ ጊዜ ድረስ የደረሰውን አደጋና ሊቃጣ የታሰበውን ሁሉ ቀድመህ ስለተረዳህ ልታስረዳኝና ልታስቀረኝ ሞከርክ። እኔ ደግሞ እንደአደጋ የቆጠርኩት ትምህርቴን ማቋረጤን እንጅ እንደዚህ ወድቄ መቅረት እንደምችል አልተረዳሁም ነበር። እግዚአብሔር የፈቀደው ስለሆነ አንተ እየፈራህ፣ ልጅ በህይወት ቆይልኝ፣ አንች ህይወትሽ ይቆይልኝ እንጅ ትምህርቱ ይደርሳልና እባክሽ ቅሪ እያልክ አልቅሰህ እየለመንከኝ አሸንፌህ መጣሁ። መጥቸም የፈራኸውን ሁሉ መከራ ተቀበልኩ።

እኔም አሻፈረኝ ብየ መጥቼ አማራና ክርስቲያን በመሆኔ ብቻ ለዚህ በቃሁ። እኔና የታፈኑት መሰል ጓደኞች ምንም ጥፋት ሳናጠፋ በጨካኞችና በአረመኔዎች እጅ ወደቅን። እንደተያዝን አካባቢ ከታፈኑት ተማሪዎች ጋር አብረን በቆየንበት በዚያ በአጭር ጊዜ እንደእኔ በሸፍጥ የታጀለው የኦሮሞ ፓለቲካ ያመጣው ጣጣ ለዚህ ያበቃቸው መሆኑ የገባቸው ጥቂቶች ነበሩ። ብዙዎቹ ግን መንግስት ደርሶ ያስፈታናል፤ የኢትዮጵያ ህዝብ አስችሎት አይተወንም፤ አዴፓ ልጆችን ብሎ ተፋልሞም ቢሆን ነፃ ያወጣናል፤ በዶ/ር አብይ መንግስት ይህ ወንጀል ተቀባይነት የለውም ወ ዘ ተ እያሉ ባለተስፋ ነበሩ።

አባባ አንዳንዶቹ ጓደኞቸ በሚያሳዝን ሁኔታ ኢህዴግ ስሙን ቀይሮ ብልፅግና መሆኑ የጉልቻ መቀያየር መሆኑን አልተገነዘቡም ነበር። ከብአዴን ወደአዴፓ ስሙን የቀየረው የአማራ ተወካይ ነኝ የሚለው የአማራ ሸክም፤ የአማራ የመከራ ዱላ፣ እድሜ ልክ አድርባይ መሆኑን እንኳን ተማሪዎቹ ህዝቡም የተረዳ አይመስለኝም።

አባባ በነገራችን ላይ እነዚያ አብረውኝ ታፍነው የተወሰዱት ጓደኞቸ በአጭር ጊዜ አብሮነታችን የሚጠሩኝ “የእኛ” ብለው ነበር። “የእኛ” ብለው የጠሩብኝ ምክንያትም የተያዝን ሰሞን ከሌሎቹ በተለየ ደጋግሜ ”የኦሮሞ ፓለቲካና የእኛ እጣ ፈንታ እንዲህ ሁኖ ይቅር” ማለት ሳዘወትር ስለሰሙ ነበር።

እኔስ እድሜ ላንተ ዘግይቸም ቢሆን እኛን የማጥፋት ደባ እንዳለ ስለተረዳሁ ምክርህን ሰምቼ ለመጠቀም ባልታደልም፣ አደጋ ላይ ስንወድቅ ተስፋ ያደረግኩት መንግስትም ሆነ ባለስልጣን አልነበረኝም። እናንተም አቅም ኖሯችሁ ልጆቻችሁን ታግላችሁ ታስፈታላችሁ ብየ አላስብም። ምናልባት ከእኛ ውስጥ ተርፎ ለወሬ ነጋሪነት የሚበቃ ተማሪ ካለ በተአምርና በእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ ነው። እኔም ያኔ ሀሳብህን ተቃውሜ እምቢ ያልኩህ እንደሌሎቹ ሁሉ ባልበሰለ ጭንቅላት ደግ ደጉን ስለማስብ ነበር። አንተ ቀድሞ የገባህ የፈራኸው ነገር እንደነበረ ማገናዘብ ባለመቻሌ አባቴ ይቅር በለኝ።

የትም ወድቆ መቅረት፣ ይቀጥላል።

ዘውዲቱ የማነ

2020-10-16